የሙስሊማችን ቅዱስ ወር የረመዳንን ማሳረጊያ የ Eid al-Fitr ን በዓል ለምታከብሩ ለእስልምና ዕምነት ተከታዮች ሁሉ ይህንን መልዕክት ሳስተላልፍ በደስታ ነው። ረመዳን በቅዱስ ቁርዓን የእግዚአብሔር ቃል ለነቢዩ መሐመድ የተገለፀበት፥ የሚታወስበት፥ ቃሉ በጽሞና በምህላ የሚነበብበት ወቅት ነው። ባለፈው ወር፥ ሙስሊሞች ሐሳባቸውን ወደ እምነታቸው፥ ልባቸውን ወደ ምጽዋት ለማትኮር፥ ቀኑን ያለ ምግብና ውሃ በጾም በጸሎት አሳልፈዋል። በዓለም ዙሪያ ያሉ ሙስሊሞች፥ የምሕረት እጃቸውን ዘርግተው፥ የተቸገሩትን ረድተዋል።

በየከተሞቹ፥ ድሆች ጾማቸውን የሚፈቱበት ተዘጋጅቶ፥ ሁሉም የእግዚአብሔርን ስጦታ ተካፋይ እንዲሆኑ፥ ምግብ፥ ልብስና ገንዘብ ታድሏል። ሙስሊሞች መቻቻልን በማሳየት፥ ብዙውን ጊዜ በበዓሉ ቀን የሌሎች እምነት ተከታዮችን Iftar ወይም እራት እቤታቸው ይጋብዛሉ።

በ Eid al-Fitr ሙስሊሞች ጾሙን መፍታትና አብሮት የሚመጣውንም የእምነት ተሃድሶ ያደርጋሉ። በየአገሮቹ፥ እንደባህሉ አከባበሩ ይለያያል። ከግብጽ ፋኖስ ማብራት፥ እስከ ፓኪስታን ርችት ትኩሳ። በዓለም ዙሪያ ቤተሰብ፥ ጎረቤት፥ ወደጅ ዘመድ ተሰብስቦ ለበዓሉ የተዘጋጀውን እየተመገበ እንኳን አደረሳችሁ ይባባላል።

የዚህ በዓል መንፈስ፥ እስልምና በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ለሀገሬ ሰዎችና በዓለም አካባቢ ለሚገኙ ከአንድ ቢሊዮን በላይ ለሚሆኑ ተስፋ እንደሚሰጥ ያስታውሰናል። በረመዳን፥ እስልምና ለሰው ልጅ ጠቀሜታና ሥልጣኔ ያበረከተበትን የምናስታውስበት ወቅት ነው።

እዚህ በዩናይትድ ስቴትስ፥ ሙስሊሞች በቢዝነስ፥ በሕግ፥ በመድኃኒት፥ በትምህርትና በሌላም መስክ፥ ብዙ አስተዋጽዖ አድርገዋል። ሙስሊሞች የጦር ኃይሎች አባሎቻችን በኔ አስተዳደር ውስጥ ያሉትም፥ ሰላም በሰፈነበት ዓለም፥ ሀገራችን የቆመችለትን ዓላማ፥ ነፃነትና ፍትሕ በማስከበር አሜሪካውያን ወገኖቻቸውን ያላንዳች እንከን ያገለግላሉ።

በአሜሪካና በሌላውም ዓለም ለምትገኙ የእስልምና እምነት ተከታዮች፥ ከ Laura ጋር መልካም በዓል ይሁንላችሁ እያልን ምኞታችንን እንገልጻለን። በረመዳን ወቅት የተቀበላችሁት ቡራኬ ዓመቱን አብሯችሁ እንዲቆይ እንመኛለን።